# የኢሕአፓ 8 ድንቅ ባሕሪያቱ

ክጸጋው ዘለቀ

***ይህ ጽሁፍ የግለሰብ ግንዛቤ እንደሆነ በቀድሚያ እንዲያሰምሩበት እጠይቃለሁ!!!***

ዘንድሮ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ መብት የሰፈነ ይመስል የፓለቲካ ድርጅቶች እንደአሸን ፈልተዋል:: ለአገርና ለሕዝብ ነው የምንታገለው የሚል ፕሮግራም ይነድፋሉ:: ሆኖም ግን ጠጋ ተብለው ሲፈተሹ ያንዳንዶቹ ተልእኮ የጻፉትን የሚቃረን ሆኖ ነው የሚገኘው:: አንዳንዱ በድርጅት ስም ገንዘብ ለማካበት ነው የተሰማራው:: የተወሰኑት ደግሞ ለግል ስም ሙግሰና ሲሆን ቁጥራቸው የማይናቅ ደገሞ ወገበ ሰባራ የሆነውን ወያኔን ቅዱስ ለማድረግ የቆሙ  ሆነው ነው የምናገኛቸው:: ጥቂት እንኳን ቢሆኑም ጠንካራና ሕዝባዊ የሆኑ ድርጅቶች መኖራቸው አያጠራጥርም::  ሆኖም ግን እስከዛሬ ድረስ ካስተዋልኳቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በቆራጥነት ለኢትዮጵያ ደሙን ያፈሰሰ ጀግና ድርጀት ኢሕአፓ ስለመሆኑ ያላንዳች ማመንታት መናገር እችላለሁ:: አባባሌንም በሚሊዮኖቹ የሚቆጠሩት ኢትዮጵያውያን እንደሚጋሩኝ የቅንጣትም ያህል ክልጠራጠርም::

ኢሕአፓ የሶስት ጉደኛ ገዝዎችን ተመልክቷል:: የኢትዮጵያን ድፍን ሕዝብ በባርነት መልክ ቀፍድዶ የገዛውን የፊዳል ስርአት አራማጁን የሓይለስላሴን አገዛዝ፡ አንድ ትውልድ የፈጀውን የፋሺስቱ መንግስቱ ሃይለማሪያምን፡ የዘንድሮዎቹን እጅግ በጣም ጠባብ ብሔርተኛ መንግስት ቁንጮ የሆነውንም የመለሰን አገዛዝ በአርምሞ እያስተዋለው ይገኛል:: ማየትና ማስተዋልም ብቻ ሳይሆን  ሁሉንም በሚገባ ታግሏለ እየታገለም ይገኛል፡፡ ኢሕአፓ ከሁሉም የፓለቲካ ድርጅቶች ልዩ የሚያደርጉት በርካታ ባሕሪት ቢኖሩትም ይህ ጽሁፍ ለያተኩር የፈለገው ግን  በስምንቱ  ደንቅ ባሕሪያቱ ላይ ብቻ ይሆናል::

## 1. ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር የማያጠያይቅ አቋም አለው

ኢሕእፓ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ዙሪያ ድንበሯንና መለያ ሰንደቃላማዋን በጠላት ላለማስደፈር ደሙን ገብሯል:: ወያኔና ሻቢያ (ኦኤለፍንም ጨምሮ) የኢትዮጵያ ታሪክ 100 ዓመት ነው ሲሉ ኢሕአፓ ሳይታክት በመታገል የኢትዮጵያ ታሪክ በሺዎቹ አመታት ስለመቆጠሩ አስተምሯል:: ላገርና ለሕዝቧ የበላይነት ባያሌ የሚቆጠሩ አባላቱን ሕይወት ገብሯል::  ***እናት የሞተች እንደሆን  ባገር ይለቀሳል አገር የሞተ ለት ወዴት ይደረሳል****?* *የሚለው አባባል*  በውል የተረዳሁት በዚህ በዘንድሮው የወያኔ ዘመን ነው ብል አልተሳሳትኩም:: አገሩን እንደቅርጫ መትረው በመከፋፈል ኢትዮጵያዊ ስሜትን ሰልበው የተልፈሰፈስ ትውልድን ለመፍጠር ሽርጉዱን ከተያያዙት ዘመናትን ቢያስቆጥሩም በእንደኢሕአፓ መሰሉ ጀግናና የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆቿ ተጋድሎ ያጥፊዎች ምኞት የፈለጉትን ያህል ሊሰምር ባለመቻሉ ደስታዬ ወሰን የለውም:: ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር ባለው ጠንካራ አቋሙ ኢሕአፓ በተገንጣዮች በተለይም ከወያኔና ከሻቢያ የተወረወረበት ጦር የሁለት ሶስት አገሮችን የጦር ሰራዊት የሚያፈርስ ቢሆንም ኢሕአፓን ግን ሊያፈርሱትም ወይም ላገሩ ያለውን ፍቅር ሊቦረብሩት አልቻሉም:: ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር ያደረገውን እያደረገ ያለውን የጀግንነት መስዋእትነት የሚያስከብረውና በታሪክም ልዩ ስፍራ የሚያስጠውም ነው::

## 2. <u>ለመብትና ለዲሞክራሲ መስፈን ሳይድክም ዛሬም መታገሉ</u>

ኢህአፓ ገና ከጅምር መሰረቱ የቆመው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበርና ለዲሞክራሲ የሚታገል ስለመሆኑ ምስክሩ ታሪ በጥቂት ስም አጥፊዎች አሉባልታ ሕዝቡ መፈታት የለበትም ። ኢሕአፓ ስለዲሞክራሲና ፍትህ በሰፊው ለሕዝቡ አስተምሯል። ታግሎም አታግሏል። ዛሬም ይህ ጥያቄ አልተመለሰምና ከማንኛውም ድርጅት የበለጠ በነዚህ መፈክሮች ዙሪያ የመረረ ትግል እያካሄደ ይገኛል። ለተሸራረፈ መብትና ለተለሳለሰ ዲሞክራሲ የሚሰብኩትንም አምርሮ ይታገላል። ደርግን ጨካኝ ያደረገው ኢሕአፓ ነው ሲባል ሰምተን “አህያውን ፈርቶ ዳውላው” ሆኖብን ማዘንም መሳቅም መምረጡ ያስቸገረን ሰዎች ጥቂት ባንሆን የሚደንቅ አይደልም። ዛሬ ደግሞ ይህም መንግስት አገር አፍራሽ ነው፤ ጸረ-ዲሞክራሲና እምባገነን ነው ብሎ ኢሕአፓ ሕዝቡን ለትግል በሚያነሳሳበት ጊዜ የለም ለምነና ዋስትና ፈርመን ከወያኔ ጋር በመሰራት ዲሞክራሲን ልናመጣ እንችላለን የሚሉ “ዲሞክራሲያዊ ዲሞክራቶች” (ወይም ከኢሕአፓ የፈረጠጠው አንጃ) ሲሯሯጡ እያየ ቸው ነው። አንዳንዱ (ድርጅትም ይሁን ግለሰብ ) ስለ መብትና ዲሞክራሲ ምንነት በውል አለመረዳቱን ለማወቅ ችለናል። መብትና ዲሞክራሲያዊ ነጻነታችንን በልመና፤ በመፈረም፤ በማጎብደድና በመለማመጥ ከወያኔም ሆነ ከማንኛውም አንባገነን ገዥ ማግኘት ከቶም አለመቻሉን ከኢሕአፓ በላይ የተረዳ ድርጅት ካለ መልካም። በመሰረቱ መብትንና ዲሞክራሲን መለመንና በጉልበታችን ማስከበር ለየቅል ናቸው። ለዚህም ነው ኢሕአፓ መብቴንና ዲሞክራሲ ነጻነቴ ለምኜ ሳይሆን ባመጽ ነው የማገኘው በማለት ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወሳኙ ድል ማዘጋጀቱ ላይ ጫና የሚሰጠው።

## 3. <u>ኢሕአፓና</u> <u>ሁለ-ገብ የትግል ስልቱ ልዩ ምልክቱ ነው</u>

ለአገርና ለሕዝቧ አንድነት የሚደረግ ትግል ጨዋታ (*ዳቦ ተቆረሰ ጨዋት ፈረረሰ*) አይደለም። ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን የመረጠው የትግል ስልት ሁሉ-ገብ የትግል ስልት መሆኑን ያሳየው ዛሬ ሳይሆን ካፈጣጠሩ ጀምሮ ነው። ስንትና ስንት ዘመን ካለፈ በኋላ ትግሉ መሆን ያለበት ሁለ-ገብ ነው ብለው እንደ አዲስ ግኝት ሊሰብኩን የሚፈልጉትን የግንቦት 7 መሪ ዶክተር የትግሉ ዘዴ ስለተገልጸላቸው እየተደሰትን ግን ዘዴው ማታገያና ሕዝብን ለስልጣን ማብቂያ እንጂ ገንዘብ መለመኛ አዲስ ዘዴ አለመሆኑን መገንዘብ አለባቸው። ኢሕአፓ በሰላሙና ባመጹ የትግል ስልት ተጠቅሞ እጅግ አመርቂ የሆነ ውጤትን አስመዝግቧል። ይህን የሚጠይቅ ካለ ታሪኩን መመልከት ተገቢ ይሆናል። ኢሕአፓ ይህን ሁሉ-ገብ ትግል መታገያው ያደረገው የዛሬ ሰላሳዎቹ አመት እንጂ የዛሬ ሁለት ወር አለመሆኑን የግንቦት ሰባቱ ዶክተር ቢያውቁት (ያውቁታል) ቀና ያደርጋቸዋል።

ስለ ሰላም ትግል ከኢሕአፓ የበለጠ የሚረዳ ኢትዮጵያዊ የፓለቲካ ድርጅት ስለመኖሩ እሰጣ ገባ ባልገባም ግን ይህ ድርጅት ምንኛ የሰላሙን ትግል እንደሚያስተምርና ተግባራዊም ለማድረግ እንደሚሞክር የማይረዳ ካለ ዋሾና አደናጋሪ ብቻ ነው ማለቱ ከሃቅ የራቀ አይሆንም። ስለሆነም እኮ ነው የሰላማዊ ትግል ጭላንጭል በታየበት ሁሉ ኢሕአፓ ኢሕአፓ የሚሸተው። ጠላት ግን ሰላምን እንደማይፈልግ ለኢሕአፓ ሁሌም ግልጽ ነው። በተለይ ወያኔ ያለ አመጽ በሰላም ይወድቃል ማለት ኩል ከመሰለ የጠራ ሰማይ ዝናብ ይወርዳል ብሎ የመጠበቅ ሞኝነት ይመስላል። ለዚህም ነው ወያኔን በሰላም ትግሉ ብቻ ከስልጣን ማውረድ የማይቻል ሞኝነት የሚሆነው። ስለሆነም ነው ኢሕአፓ ጊዜ የማይሽረውን የሁለ-ገብ ትግል የሚያራም። ይህ የትግል ስልቱ ለኢሕአፓን ልዩና ጠንካራ ባህሪው ነው።

## 4. ኢሕአፓ በደም የተፈተነ የፓለቲካ ድርርጅት ነው

ወርቅ በሳት እንደሚፈተን ሁሉ ኢሕአፓም በመከራ በሰቆቃ በስራትና በሞት የተፈተነ ድርጅት እንጂ እንደሌሎቹ አልጋ ባልጋ የተሸጋገረ ድርጅት አይደለም፡፡ እንደ ሕዝቡ ተርቦ፣ ታሞና ሞቶ ነው መሰዋእትነት እየከፈለ ያለው እንጂ የደላው ድርጅት አይደለም፡፡ አባላቱ ይህ ነው የማይባል ድንቅ መስዋዕትነትን ከፍለዋል፡፡ ያመራር አባላቱም ለኢትዮጵያ፡ ለሕዝብቧና ለድርጅቱ ሲሉ ልክ እንደ ቴዎድሮስ እምቢኝ በማለት ለጠላት እንኳን ግራ በሚያጋባ ሁኔታ መስዋዕትነትን ከፍለው ያለፉት፡፡

በፋሺስቱ ደርግ መንግስት ዘመን የታጨደውን ወገን ቤቱ ይቁጠረው፡፡ በወያኔ ሴራ ለሰለባ የተዳረጉት ጀግና የኢሕአፓ አባላት ቁጥርም ተቆጥሮ የሚዘለቅም አይደለም፡፡ ባጭሩ ላለፉት 36 አመታት በኢሕአፓ ላይ ከየአቅጣጫው የወረደው ጭፍጨፋ ኢሕአፓ እንደ ብረት አጠነከረው እንጂ አላጠፋውም፡፡ ብዙዎቻችን የእድሜ ባለጸጋዎች ሆነን ሶስት መንግስታትን አይተናል፡፡ ያፍና የወረቀት ላይ ነብሮችንም አስተውለናል፡፡ እናንተ ሞታችሁልን እኛ መሪነቱን እንያዝ ያሉትንም ሞኛሞኞችም ተመልክተናል፡፡ ሕዝባችንን ደጋግመው የከዱትንም ከንቱዎችንም ሳንወድ ተመልክተናል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የገረፉን ያሰሩንና ወገናችንን የገደሉትንም መሪ ካለኛ የለም ብለው እየፎከሩ ያሉትን ሁሉ እያየ  ነው ያለነው ቀን እስኪያልፍ ድረስ፡፡

ለኢሕአፓ ምስጋና ይግባውና ታሪካቸውን ቁልጭ እያደረገና እያጋለጠለን ይገኛል፡፡ የሰንቱን ኢሕአፓ አባላትን ሰውነት በሳት ጠብሰዋል? የሰንቱን ወጣት ጣቶች ቆርጠዋል? የስንቱን ጀግና ሕይወት መትረዋል? የሞቱት  ሙተው  የተረፉት ደግሞ በግርፋት በእስራትና በስደት የከፈሉትና እየከፈሉ ያሉት መስዋዕትነት ኢሕአፓን ልዩ ካላደረገው ማንን ልዩ ሊያደርግ?

## 5. ኢሕአፓ በጋራ መታገልን ከማንኛውም ድርጅት የበለጥ ያምንበታል

ገና ከጠዋቱ እንደዛሬው “ተራማጅ” ነኝ የሚለው ሳያታክተን ኢሕአፓ ለብቻው ሆኖ አብሮት ከትግሉ ጎራ የሚሰለፍ ድርጅት በመፈልግ ደክሟል፡፡ እንኳን ከሚደግፉት ከሚገድሉትም እንካን ያኔም ዛረም እንደሚሰራ በተግባር አሳይቷል፡፡ ኢትዮጵያን ከዛሬዎቹ ገዝዎች ለማዳን ይገድለው ከነበረውም ከደርግ ጋር ግንባር በመፍጠር አገሪቷን ለማዳን እንደሞከረ ታዛቢ ኢትዮጵያውያን በቁጭት የሚዘክሩት ነገር ነው፡፡ ከደርግ ባላነሰ መኢሶንና የአረጋዊ በርሔ ወያኔም  ኢሕአፓን ጨፍጭፈውታል፡፡ ሆኖም ግን ሳገር ሊበጅ ይችላል ከማለት ካረዱትም ጋር አብሮ ተጉዟል፡፡ ኢሕአፓ ስለ ጋራ ትግል መታገሉ ከማንኛውም ኢትዮጵያው ድርጅቶች የላቀ ስፍራ ያሰጠዋል፡፡ ካማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ልዩ ከሚያደርጉት ይህ ባህሪው አንዱ ነው፡፡ ለዋቤነት እንዲሆን ስለ ኢድሐቅና ያጎረሰ እጅ ነካሽ የሆነውን ህብረት ማስተዋሉ በቂ ነው፡፡

## 7. ኢሕአፓ ለሕዝ ወዳጅ ሚች ለጠላቱ ግን  የእግር ውስጥ እሳት ነው

ሊሰመርበት የሚገባው አነጋገር ነው፡፡  ዛሬ ብዙ የዋሕ የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅትነን ባዮች  ጠላትን ወዳጅ ወዳጅን ጥላት አድርገው እንደሚፈርጁ አስተውለናል፡፡ ባለማወቅም ሊሆን ቢችልም በተለይ ሆን ብለው ይህን አካሄድ ትክክል ነው ብለው ሌት ተቀን የሚፈጉ ማየታችን አልቀረም፡፡ ለጊዜው ያደናግሩናል እንጂ የትም እንደማይደርሱ እናውቀዋለንና ብዙም ሊደንቀን አይገባም፡፡ የሆኖ ሆኖ ግን ልደርባይ ድርጅቶችን ለይቶ ማወቁ ብልህነት ነውና ማን እውነተኛ ማን አደናጋሪ ድርጅተ ስለመሆኑ መማር ካስፈልገ ጆሮንና አይንን ወደ ኢሕአፓ በማድረግ

የማይከፈልበት ሕዝባዊ ተመክሮ ማግኘት መሞከሩ ብልህነት እንጂ ደካማነት አይደለም።

ኢሕአፓ የደርግን አጥፊነት በሚገባ ተረድቶ ምልአተ-ሕዝቡን ከጎኑ አሰልፎ የሞት የሽረት ፍልሚያ በሚያደርግበት በዚያ ክፉ ወቅት ደርግን የሕዝብ ወገን አድርገው ይሰብኩ የነበሩ አውቆ አጥፊዎችን ከስህተታቸው እንዲማሩ ቢሞከርም አልሰማ ብለው የማይሆን እጠፋፍ ሲጠፉ እይተን ቢያንስ እዝነንላቸዋል። ወያኔ ደግሞ በኢትዮጵያዊነት ላይ ያለውን ክፉ አመለካከት ለሕዝቡ ኢሕአፓ ሲያስደምጥና ሲታገል አንዳንድ ምሁር ነኝ ባዮች ከስማቸው በፊት የትምህርት ታርጋቸውን በመለጠፍ ሕዝቡን ሲያወናብዱ ተስተውሏል። የሚገርመው ግን ለወያኔ አለሁልህ የሚሉ ሁሉ ከወያኔ ያገኙትና እያገኙ ያለው ውርደትን ብቻ መሆኑ ነው። ይበላቸው!!

ኢሕአፓን ልዩ የሚያደርገው ጠላቱንና ወዳጁን በሚገባ ለይቶ ማወቁ ነው።እንኳን የሩቆቹንና አብረውት የነበሩትን ከሃዲያንን ገና ማርሽ ለመቀየር ሲመቻቹ ነቅቶ በመጠባበቅ አንይሆኑ ሆነው በርግገው መፈርጠጣቸውን ተመልክተናል። ጠላትና ወዳጅን ማወቅ ልዩ ችሎታን አይጠይቅም። በኢትዮጵያዊነት ላይ ያለን እምነት የጠነከረ ከሆነ ማን ጠላቷና ማን ወዳጇ ስለመሆኑ ሌላ መስፈርት ከቶም አያሻም። የኢትዮጵያን የብዙ ሺህ ዘመን ታሪኳን የመቶ አመት ያደረገ፣ የመለያ አርማዋን ጨርቅ ነው ብሎ የረገጠ፣ ድንበሯን በጭብጨባና በደስታ ሳይጠይቁት የሚሰጥ፣ የሕዝቧን መብት የገፈፈ . . . ጠላት ካልሆነ ምን ሊሆን እንደሚችል ልዩ መልስ ሊሰጡን የሚችሉት አድርባዮችና ካሃዲዎች ብቻ ናቸው።

ጠላቱን የማያውቅ ወዳጁን ጠላት ያደርጋል ሆኖ ዛሬ ከጎናቸው ሊሰለፍ የሚችለውን ኢሕአፓን ከጠላት ፈርጀው ሲታገሉት ማየቱ ከማሳዘኑም ባሻገር እንዴት ሰው ወዳጅና ጠላቱን መለየት ያቅተዋ የሚልም ጥያቄ ውስጥ ያስገባል። ስለ ደርግ ነብሰበላነት ኢሕአፓ ለመኢሶን ቢነግረውም ካለመቀበሉ ሌላ ከደርግ ወግኖ ስንቱን ለጋ ወጣት መፍጀቱን ባይናችን አይተናል። የማይቀር ሃቅ ሆነና ግልጋሎቱ ሲያበቃ ደርግ መኢሶንን እንደ ሸንኮራ አገዳ ምጣጭ አሽቀንጥሮ ጥሎታል። ቅንጅቱና ሕብረቱ ውስጥ የነበሩ ከወያኔ ጋር መስራት ይቻላ ሲሉ ኢሕአፓ እንደማይሆን ቢነግራቸውም አልተቀበሉትም። ግርግሩ ሲሰክን ዛሬ የተገነዘቡት ወንበር እማቂ መሆናቸውን ነው። ወያኔን በሰላማዊ ትግል እንጥለዋለን ያሉትን ቅንጅቶችንንም መከሮ ባለማዳመጣቸው ቤታቸው ከርቸሌ ሲሆን አልተደነቅንም። ያኔ ኢሕአፓን ይኮንን የነበርው የዛሬው የወረቀት ላይ ነብሩ ዶክተር ከኢሕአፓ ተምረናል ላለማለት ሁለ-ገብ ትግል ስልት አዲስ የተገለጸለት የትግል ስልት ስለመሆኑ ከአሜሪካን ተራራዎች ላይ ሆኖ ነግሮናል። የበርካታ ድርጅቶች ስህተት ኢሕአፓን የተመክሮ ባለጸጋነት ለመቀበል ከመፍራቱ ላይ ነው።

## 8. ኢሕአፓ ከጠባብና ከትምክህተኛ ብሄርተኝነት የጸዳ ድርጅት ነው

እጅግ በጣም ጠቦ ወይም በትምክህተኝነት ያንድን አካባቢ ሕዝብ በብሔርተኝነት ዙሪያ በማሰለፍ ፈጣን ግን ጊዜያዊ የሆነ ስልጣን መያዝ እንደሚቻል በሌሎች አገሮችና በኛም አገር እያየነው ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚሸረበውንና የተደረገውን ጥፋት ስንቃኝ በብሔርተኝነት(ጠባቡም ይሁን ትምክህተኛው) ላይ የተመሰረተ የሕዝብ ትግል ነጣይነት እንጂ አሰባሳቢ ሊሆን ከቶ እንደማይችል ነው። በዚህ ትግል ዙሪያ ገና ከመሰረቱ በኢሕአፓና በወያኔ ብሎም በሌሎቹም ብሄርተኛ ቡድኖች መካከል መቅደም ያለበት የብሄር ጥያቄ ነው ወይስ የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው የሚለው መሰረታዊ ጉዳይ ላይ የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት ታይቷል። ኢሕአፓ ቀዳሚ መሆን የሚገባው የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው ሲል ወያኔና መሰሎቹ አገርን እንደ

ዳቦ በመቆራረጥ ለብሄርተኛ ጥያቄአቸው ቅድሚያ ሰጥተው ዛሬ ካለንበት አሳፋሪና አዋራጅ ዘመን ላይ ደርሰናል። ዛሬ የትግራይ ሕዝብ ከወያኔ ያገኘው የዲሞክራሲ መብት ጭላንጭሉም ባይታይ መረገም ያለበበት ኢሕአፓ ሳይሆን ጠባቡን ብሔርተኛ ወያኔን ነው። ኢሕአፓ በወያኔና በትግራይ ሕዝብ መካከል ያለውን ልዩነት በውል ይረዳዋል። በርግጥ ወያኔ የሆነ ሁሉ የትግራይ ተወላ ሲሆን በተቃራኒው ግን የትግራይ ተወላጅ በሙሉ ወያኔ ጅነው ማለት አይደለም። የትግራይ ተወላጅ በሙሉ ወያኔ ነው ብለው የሚያክቸለችሉትን ግለስቦችንና የፓለቲካ ድርጅቶችንም ኢሕአፓ ያርማል።

ኢሕአፓ የብሄር ጥያቄን የሚያከብር ግን ለኢትዮጵያ የሚበጃት ደግሞ በብሄር መታገል ሳይሆን ሁሉንም ነጻ የሚያወጣውን የዲሞክራሲያ መብት መከበርን ሊያጎናጽፍ የሚችለውን ትግል ማፋፋም ነው ብሎም በጽናት እየታገለም ይገኛል።

## በመጨረሻም

በርግጥ ጠላቶቹ በርካታ ናቸው። ይህ ደግሞ የሚጠበቅም ነው። ሆኖም ግን ኢሕአፓ ዕውነተኛና የቁርጥ የኢትዮጵያ ልጅ በመሆኑ ማንም ከህዝቡ ነጥሎ የሚያወጣው አንዳችም ምድራዊ ሓይል የለም። የደርግ፥ የወያኔ፥ የሻቢያ ጦርም አልፈታውም። ከውስጥ ቦርቡረው ሊጥሉት የተነሱትን አንጀኞችን በተደጋጋሚ አውልቆ ጥሏቸዋል።

ላለፉት 36 አመታት የዚሕን ድንቅ ድርጅት ታሪክ በሚገባ ተከታትየዋለሁ። ስለ ልዩ ባህሪያቱም ማውራት የደፈርኩት ታሪኩን በመከታተሌ ነው። ኢሕአፓ በቃላት ብቻ ሳይሆን የማመሰግነው የጀመረውን ሕዝባዊ ትግል ከግቡ ኢስኪያደርስ ድረስ በገንዘብም በሞራልም አግዘዋለሁ። ይህ ድርጅት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታና መከታ በመሆኑ የሁላችንም እርዳታ ያስፈልገዋልና ጎበዝ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፣ ባለእውቀቱ በእውቀቱ፣ ትብብሩንና ድጋፉን ሊሰጠው ይገባል።

ኔኢሕአፓ ጋር እናብር!!!!